የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 4
ADDIS ABABA - 23rd October, 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፺፪/፲፱፻፺ ዓ·ም·
በገቢ እና በካፒታል ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................... ገጽ ፮፻፵፭

CONTENTS

Proclamation No. 92/1997
Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect Taxes on Income and Capital between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the state of Kuwait Ratification Proclamation ...................... Page 645

## አዋጅ ቁጥር ፺፪/፲፱፻፺

## በገቢና በካፒታል ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥታት መካከል በገቢ እና በካፒታል ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ በኩዌት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በገቢ እና በካፒታል ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፺፪/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## *PROCLAMATION No. 92/1997*

## *A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE STATE OF KUWAIT FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME AND CAPITAL*

*WHEREAS,* an Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income and Capital was signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait, in Kuwait, on the 14th day of September 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said agreement at its session held on the 23rd day of october, 1997;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income and Capital between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait Ratification Proclamation No. 92/1997."

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥታት መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ኩዌት ላይ የተፈረመው በገቢ እና በካፒታል ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income and Capital between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait signed on the 14th day of September 1996, is ratified.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned governmental organs.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 23rd day of October, 1997.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of October, 1997

*NEGASO GIDADA (DR.)*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING INTERPRISE